# መጽሐፍ ቅዱሳዊ የፈውስ ጥቅሶች
# Healing Scriptures

## በሲድ ሮዝ ተመርጠውና ለግላችሁ እንዲሆኑ ለእናንተ ተዘጋጁ



“ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ መርምሬአለሁ እናም እጅግ በጣም ኃይለኛ የፈውስ ጥቅሶችን በአንድ ምቹ ቦታ ሰብስቤአለሁ።

አሰላስሉአቸው እና በሕይወታችሁ ላይ በየቀኑ ጸልዩአቸው!”

-ሲድ ሮዝ፥

Sid Roth’s
IT’s SUpERNaTuRaL!™
& MEssIanIc vIsIoN

# ገጽ ማውጫ

ቃል ከሲድ........................................................................................ 2

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዴት ነው የምናሰላስለው............................................ 3

የፈውሳችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር................................................ 6

የበረከት ጸሎት.................................................................................. 29

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መግለጫ........................................................... 30

እንድታነቧቸው የሚመከሩ ምንጮች.......................................................... 31

ታሪካችሁን አካፍሉ............................................................................ 32

# ቃል ከሲድ

ፈውስ እና እምነት ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች ምስጢራዊ እንደሆኑ አውቄአለሁ። በእነዚህ ርዕሶች ላይ ብዙ መጽሐፎች ያሉ ቢሆንም፥ እነርሱ አሁንም እንደተደናገሩ ቆይተዋል።



የራሴን ሪሰርች(ጥናት) የጀመርሁት ከ40 ዓመታት በፊት ነበረ። ምርጡን ያገኘሁት የራሴን ጥናት በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ላይ ሳደርግ ነበር። በቅድሚያ፥ የእምነት እና የፈውስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን በሙሉ ዘረዘርሁ። ከዛ፥ ረጅሙን ዝርዝሬን አጠር በማድረግ በሚገባ አዘጋጀሁት። በመቀጠል፥ ቀሪዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለግል እንዲሆኑ አደረግኋቸው። በመጨረሻ እነርሱ ላይ ማሰላሰል ጀመርሁ።

ይህ eመጽሐፍ (eBooK) የግሌን የመጽሐፍ ቅዱስ የፈውስ ዝርዝር ይዟል። እናንተ በእነዚህ የተስፋ ቃሎች ላይ ስታሰላስሉ፥ ከጭንቅላታችሁ(ከራሳችሁ) ወደ ልባችሁ ይወርዳሉ። ይህ እናንተ ከአዕምሮ ስምምነት ወደ እምነት ስትቀይሩ ነው (በዚህ ጊዜ ነው ከአዕምሮ ስምምነት ወደ እምነት የምትቀይሩት)። ይህ ሲሆን፥ መንግሥተ ሰማይ ወደተባለው ከተፈጥሮበላይ ወደሆነው መግቢያ ውስጥ በተደጋጋሚ ታንኳኳላችሁ።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝር ላይ ስታሰላስሉ፥ እምነትና ፈውስ ከእንግዲህ በኋላ ምስጢር አይሆኑም!

# መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዴት ነው የምናሰላስለው

**“ማሰላሰል”** በዕብራዊ ቋንቋ “መናገር ወይም ድምፅ ማውጣት” ማለት ነው። ስለዚህ፥
ለማሰላሰል የአይሁዶች ሁኔታ(ዘዴ) የእግዚአብሔርን ቃላት ከፍ ባለ ድምፅ ማጉተምተም ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሳሰላስል፥
የሚከተሉትን (በቀኝ በኩል በሳጥን ውስጥ የሚገኙትን ምሳሌዎች) አደርጋለሁ:

1) ጥቅሱን የግል ማድረግ።

2) ጥቅሱ የሚለውን ራሳችሁ ስታደርጉ በዓይነ ህሊናችሁ ማየት።

> መዝሙር 91:1 [የግል ስናደርግ]
> “የሚኖር...” [የግል ያልሆነ]
>
> እንዲህ ይሆናል
>
> “እኔ እኖራለሁ...” [የግል የሆነ]

3) ጥቅሱን ከፍ ባለ ድምፅ ተናገሩት።

4) የሚያብራሩ ቃላት ጨምሩ።

> መዝሙር 91:1 [ቃሉን ማብራራት]
> “እኔ እኖራለሁ፥ [እኔ በእርግጥ ለስለስ ያለውን የሰማይን ንፋስ ወደውስጥ እየተነፈስሁ እኖራለሁ] በልዑል መጠጊያ...”

# መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዴት ነው የምናሰላስለው

ኢየሱስን የመቅመስ እውቀት ሳይኖራችሁ ማሰላሰል ብቻ የለባችሁም ያለበለዚያ ሃይማኖታዊ ብቻ ነው የሚሆነው። እግዚአብሔርን የመቅመስ እውቀት ለማግኘት እርሱ ኢየሱስን ለኃጢአታችሁ እንዲሞት እንደላከው የግድ ማመን እና ኢየሱስን እንደ ጌታችሁና አዳኛችሁ ከፍ ባለ ድምፅ መመስከር እና ኢየሱስን ውስጣችሁ እንዲኖር መጠየቅ አለባችሁ።



መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ በማንበብ፣ በልሳኖች በየቀኑ በመጸለይ እና መሢሑ **ውስጣችሁ** እየኖረ፣ እያፈቀራችሁና እየመራችሁ እንደሆነ በቀጣይነት በመረዳት የውዳሴና የአምልኮ ሕይወት እየኖራችሁ ጥልቅ የመቅመስ(የመለማመድ) እውቀት ትቀበላላችሁ። የእርሱን ሕልውና(መገኘት) 24/7 ተደሰቱ።

እርሱን በየቀኑ በብዛት ተለማመዱት(ቅመሱት)። የእውነት እርሱን ጌታ አድርጉት። ከዛ **እናንተ በእርሱ ሙሉ በሙሉ ሙሉ እንደሆናችሁ** ግልጽ ይሆንላችኋል!

# የፈውሳችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር

# ኢያሱ 1፥7-8

እኔ ጽኑ እና እጅግ ብርቱ ነኝ። ሕግን ሁሉ ለመጠበቅ ለማድረግ ጥንቁቅ ነኝ…
ከእነርሱ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አልልም።
**በማደርገው ሁሉ** የተከናወነልኝ ለዚህ ነው። የዚህ ሕግ መጽሐፍ **በቀጣይነት** አጠናለሁ።
**በቀንም በሌሊትም አስበዋለሁ(አሰላስለዋለሁ)**…
የዚያኔ ብቻ ነው በማደርገው **ሁሉ** የሚቀናልኝና የሚከናወንልኝ።

---

# ዕብራውያን 11፥6

ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።

## ማርቆስ 11፥23-24

…ይህን ተራራ፦ ‘ወዲያውኑ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር፥’ (ብለው)፥ እያልኩት ያለው ነገር እየተደረገልኝ እንደሆነ ባምን በልቤ ሳልጠራጠር፥ ይሆንልኛል።
ለእያንዳንዱ ነገር በቀጣይነት መጸለይ አለብኝ፥ ከዛ የጠየቅሁትን ነገር ሁሉ እንዳገኘሁት አምኛለሁ፥ ለኔ ይሆንልኝማል።

## ሮሜ 10፥17

… እምነቴ ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው። [የእግዚአብሔርን ቃል እየተናገርሁ ራሴን ስሰማው እምነቴ ያድጋል እናም እግዚአብሔርን የማስደስት እሆናለሁ]።

## መዝሙር 86፥15

አቤቱ፥ አንተ ግን መሓሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ፤ መዓትህ የራቀ ምሕረትህም እውነትህም የበዛ፤

# ሮሜ 4፥17-21

…እግዚአብሔር…የሌሉ ነገሮችን[እርሱ ቃል የገባውን] [ልክ አሁን]እንዳሉ አድርጎ ተናገረ።

…[የሌሉ ነገሮችን ልክ አሁን እንዳሉ አድርጌ እጠራለሁ]

[አብርሃም] የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤

ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ **የሰጠውንም ተስፋ** ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል **አጥብቆ እየተረዳ**፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም…

## ዘጸዓት 23፥25-26

አምላኬ እግዚአብሔርን ባገለግለው (በዕብራይስጥ: “**ባመልከው**”) እርሱም እህሌንና ውሃዬን ይባርካል፤ **በሽታንም** ከመካከሌ **ያርቃል**። እርሱ የዘመኔን ቁጥር **ይሞላል**።

---

## 2ኛ ቆሮንቶስ 1፥20

እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል **ሁሉ አዎን** ማለት በእርሱ ነውና፥ አሜን በእርሱ ነው (ስለዚህ እንዲሁ ይሁን)…

---

## ኢሳይያስ 53፥4-5

በእውነት ደዌዎቼን (ሀዘኖቼን) ተቀበለ (በዕብራይስጥ: “ሥቃዮቼን”)
ሕመሞቼንም ተሸክሞአል [ወስዶአል]፤…
…በእርሱም ቁስል እኔ ተፈወስሁ።

## መዝሙር 1፥1-3

ምስጉን ነኝ (ተባርኬአለሁ) ምክንያቱም…ደስታዬ በእግዚአብሔር ሕግ ነው፥
ሕጉንም በቀንና በሌሊት አስባለሁ (ለራሴ በመናገር በጥንቃቄ አስባለሁ እምለከታለሁ)።
እኔም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥
ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ነኝ፤
**የምሠራውም ሁሉ ይከናወናል**።

## ዕብራውያን 11፥1

**እምነት**ም [እኔ] ተስፋ ስለማደርገው ነገር **የሚያስረግጥ** (የሚያረጋግጥ፣ ርዕሰ ሥራ)፥ [እኔ] **የማላየውንም** ነገር **የሚያስረዳና የእውነታው** [ለሕዋሶቼ ያልተገለጸውን የእኔ እምነት እንደ እውን ማስረጃ ይገነዘበዋል] **የፀና እምነት** ነው።

## የሐዋርያት ሥራ 10፥38

… እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም **መልካም** እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን **ሁሉ እየፈወሰ** ዞረ፥ **እግዚአብሔር** ከእርሱ ጋር ነበረና፤ [እኔ በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ተቀብቼአለሁ፥ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወስሁ መልካም አደርጋለሁ፥ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነውና]።

## ማቴዎስ 16፥19

እግዚአብሔር የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች ሰጥቶኛል፤
በምድር የማስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥
በምድርም የምፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።

[ሕመም በመንግሥተ ሰማይ ተከልክሎአል እና በኢየሱስ ስም በአካሌ እንዳይሆን ሕመሙን {ያን የተለየ ሁኔታ ጥቀሱ} እኔ ከልክዬዋለሁ!]።

## ምሳሌ 4፥20-22

የእግዚአብሔርን ንግግር አደምጣለሁ
ወደ ቃሉም ጆሮዬን አዘነብላለሁ።
ከዓይኔ አላርቃትም፥
በልቤም ውስጥ እጠብቃታለሁ።
ሕይወት ናትና፥ ለሥጋዬም ሁሉ ፈውስ ነውና።

## 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥21

እኔ በእርሱ ሆኜ የእግዚአብሔር ጽድቅ እሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኔ ኃጢአት አደረገው። [እኔ በእርሱ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነኝ!]።

## ኤፌሶን 3፥20

እንግዲህ በእኔ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምለምነው ወይም ከማስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥

## ኢሳይያስ 54፥17

በእኔ ላይ የተሠራ መሣሪያ [ሕመም የጠላት መሣሪያ ነው] ሁሉ አይከናወንም፤ …እንደ እግዚአብሔር ባሪያነቴ ርስቴ ይህ ነው…

## ዮሐንስ 10፥10

ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ [ሕመም እየሰረቀ፣ እያረደና እያጠፋ ነው]። ኢየሱስ ሕይወት እንዲሆንልኝና ሕይወትን [ጤንነትን] እንድደሰት እንዲበዛልኝም (እስከ ሙሉው ድረስ፤ ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ) መጣ።

## ማቴዎስ 28፥18-19

ኢየሱስ ቀረበና እንዲህ በማለት ተናገረ… :- “ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና… [ደቀ መዛሙርት እንዳደርግ ይህኑ ሥልጣን ተወክዬአለሁ]።”

## ሉቃስ 10፥19

እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን እረግጥ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶኛል፥ የሚጐዳኝም ምንም የለም።

## 2ኛ ጴጥሮስ 1፥3-4

የመለኮቱ ኃይል፥ የጠራንን [ሙሉ፥ በግል] በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል [አስፈላጊና ተስማሚ] የሚሆነውን ነገር ሁሉ ሰጥቶኛል… ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ስለሰጠኝ [እኔ ይህን አውቃለሁ]…

---

## 1ኛ ዮሐንስ 3፥8-9

ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። [የእኔ አላማ ትቶ እንዲሄድ ሕመምን በኢየሱስ ስም በማዘዝ ሕመምን ማፍረስ ነው]።

---

## 1ኛ ጴጥሮስ 3፥9

ክፉን በክፉ ፈንታ አልመልስም። ስድብን በስድብ ፈንታ አልመልስም። በዚህ ፈንታ እባርካለሁ እንጂ። በረከትን ልወርስ ለዚህ ተጠርቻለሁና።

# ኢሳይያስ 55፥10-12

ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ፥ ምድርን እንደሚያረካት፥
ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት፥
ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ፥

ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤
የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ [እኔ] በከንቱ አይመለስም።

እኔም በደስታ እወጣለሁ በሰላምም[ሙሉነት/ሻሎም በመንፈስ በነፍስ እና በሥጋ] እሸኛለሁ፤

## ማርቆስ 9፥23

ኢየሱስ አለ… "ማመን ከቻልህ ሁሉ ይቻላል…"

## ዕብራውያን 6፥12

… በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል እወርሳለሁ
.

## መዝሙር 105፥37

… በወገናቸውም ውስጥ ደዌ አልነበረም። [እኔ የእርሱ ቤተሰብ ነኝ!]።

## መዝሙር 107፥20

ቃሉን ላከ ፈወሰኝም፥ አዳነኝ።

## 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥7

እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠኝምና።

## ያዕቆብ 4፥7

ዲያብሎስን ግን እቃወማለሁ [ዲያብሎስን በጥብቅ እቃወመዋለሁ] ከእኔም ይሸሻል (እንደተሸበረ)።

## ኢሳይያስ 26፥3

በአንተ ታምኛለሁና ነፍሴ በአንተ ተደግፋለችና ፈጽመህ በሰላም (በሙሉነት) ትጠብቀኛለህ።…

## ሶፎንያስ 3፥17

አምላኬ እግዚአብሔር በመካከሌ
ታዳጊ ኃያል ነው
[የሚያድን/የሚፈውስ]!፤
በደስታ በእኔ ደስ ይለዋል፥
በፍቅሩም ያርፋል [በጸጥታ ደስታ]፥
በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል
ይባላል።

## ማቴዎስ 12፥36-37

… እኔ ስለምናገረው
ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ
እሰጥበታለሁ፤

ከቃሌ የተነሣ እጸድቃለሁና ከቃሌም
የተነሣ እኰነናለሁ። [ስለ ንስሐና
ስለ ኢየሱስ ደም እግዚአብሔርን
አመስግኑ!]።

## ፊሊጵስዩስ 2፥9-10

… እግዚአብሔር ኢየሱስን ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ {በሽታችሁ ስም አለው። አሁን ለዛ የድካም መንፈስ በኢየሱስ ስም ተናገሩ እና የግድ ትቶ መሄድ አለበት። በመዛል ወይም ባለማመን ተስፋ እንዳልቆረጣችሁ እርግጠኛ እስኪሆን ድረስ ይቆያል።}።

## መዝሙር 91፥9-10፤16

አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና፤ ልዑልን መጠጊያዬ አደረግሁ። ክፉ ነገር [ሕመም]ወደ እኔ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም ወደ ቤቴ አይገባም። እግዚአብሔር ረጅምን ዕድሜ ያጠግበኛል፥ ማዳኑንም [ፈውሱን] ያሳየኛል።

## ዮሐንስ 16፥23

…እውነት እውነት እላችኋለሁ፥
አብ በስሜ [እኔ እንደሆንሁ ሁሉን በማቅረብ] የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።

… ደስታዬም ሙሉና ፍጹም እንዲሆን እለምናለሁ መጠየቄንም እቀጥላለሁ እቀበልማለሁ።

# ያዕቆብ 1፥2-4፣12

ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነቴ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግልኝ አውቄ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስብኝ እንደ ሙሉ ደስታ እቆጥረዋለሁ

ትዕግሥትም ምንም የሚጎድለኝ ሳይኖር ፍጹምና ምሉዕ [ያለ ምንም እንከን/ጉድለት] እሆን ዘንድ ሥራውን በእኔ ይፈጽም። በፈተና ስጸና የተባረክሁ ነኝ (ደስተኛ ነኝ፥ የሚቀናብኝ)፤ ከተፈተንሁ በኋላ እግዚአብሔር ለምወደው ለእኔ ተስፋ ስለ እርሱ የሰጠኝን የሕይወትን አክሊል [የድል ነሺዎችን] እቀበላለሁና።

# ገላትያ 6፥9

… ባልዝልም በጊዜው አጭዳለሁና መልካም ሥራን ለመሥራት አልታክትም።

# ምሳሌ 6፥2

ዲያብሎስ በአፌ ቃል ሊያጠምደኝ ይሞክራል፤ [ከእግዚአብሔር ካለው ጋር ለመስማማት በአፌ ላይ ጠባቂ አኖርሁ]።

# 1ኛ ዮሐንስ 1፥9

በኃጢአቶቼ ብናዘዝ ኃጢአቶቼን ይቅር ሊለኝ ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻኝ የታመነና ጻድቅ ነው።

# መዝሙር 103፥2-3

ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፤

ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር የሚል፥ ደዌዬንም ሁሉ የሚፈውስ፥

# 2ኛ ቆሮንቶስ 4፥13

… አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ፥ እኔ ደግሞ አምናለሁ [ቀንና ሌሊት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ስለማሰላስል] ስለዚህም እናገራለሁ፤ …

# ዘዳግም 7፥14-15

ከአሕዛብም ሁሉ ይልቅ የተባረክሁ እሆናለሁ፤… እግዚአብሔርም ሕማምን ሁሉ ከእኔ ያርቃል…

## ሮሜ 8፥11

… ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእኔ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእኔ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነቴ ደግሞ ሕይወትን [ፈውስን] ይሰጠዋል።

---

## 1ኛ ዮሐንስ 5፥14-15

በእርሱ ዘንድ ያለኝ ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብለምን ይሰማኛል።

የምለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልኝ ባውቅ ከእርሱ የለመንሁትን ልመና እንደ ተቀበልሁ አውቃለሁ።

---

## ራእይ 12፥11

… ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክሬም ቃል [የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም በተቀበልሁ በእያንዳንዱ ጊዜ፥ የሕመምን እሥራት በስኬታማነት የበለጠና የበለጠ አጠፋለሁ] የተነሣ ዲያብሎስን [እና የእሱን የሕመም ፍሬ] ድል ነሣሁት፥ …

## መዝሙር 84፥11

በቅንነት ስለምሄድ እግዚአብሔር ከመልካም ነገር አያሳጣኝም።

## 1ኛ ዮሐንስ 4፥4

… በዓለም ካለው ይልቅ በእኔ ያለው ታላቅ ነው።

## ማቴዎስ 6፥14-15

ለሰዎች ኃጢአታቸውን [በግዴለሽና ሆን ብለው ያደረጉትን ኃጢአታቸውን ብተዋቸው፥ እንዲሄዱ ባደርጋቸው፥ ቅሬታዬን ብተው] ይቅር ብል፥ የሰማዩ አባቴ እኔንም ደግሞ ይቅር ይለኛልና፤
ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን [በግዴለሽና ሆን ብለው ያደረጉትን ኃጢአታቸውን ባልተዋቸው፥ እንዲሄዱ ባላደርጋቸው፥ ቅሬታዬን ባልተው] ይቅር ባልል፥ አባቴም ኃጢአቶቼን ይቅር አይለኝም። [ይቅር ማለት/ምሕረት አስፈላጊ ነገር ነው። ይቅር ማለት ውሳኔ ነው እንጂ ትልቅ ስሜት ወይም ስሜት አይደለም። እኔ ይቅርታ ከሚገባኝ በላይ እነርሱ ይቅርታ ስለሚገባቸው አይደለም። ይህ ማለት ሰውዬውን መተማመን አለብኝ ማለት አይደለም። እነርሱ መተማመኔን ማግኘት አለባቸው። በቅጽበት ይቅርታ-በማለት/ምሕረት-በማድረግ ለመኖር መርጫለሁ!]።

## 1ኛ ዮሐንስ 4፥17-18

… እርሱ እንዳለ እኔ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነኝና። ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ …የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።
[የእግዚአብሔር ፍቅር ፍርሃትን ይከድናል]።

## ኢሳይያስ 40፥31

እግዚአብሔርን በመተማመን ስለተጠባበቅሁ ግን ኃይሌ ታድሶአል፤ እንደ ንስር በክንፍ እወጣለሁ፤ እሮጣለሁ፥ አልታክትም፤ እሄዳለሁ፥ አልደክምም።

## መዝሙር 103፥20

ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።
[የእርሱ የተሰፋ ቃሎች በአፌ ውስጥ]።

## ዮሐንስ 20፥29

ኢየሱስም። …“…ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።”
[ከማየቴ በፊት ስላመንሁ ብፁዕ ቡሩክ ነኝ!]።

## ማቴዎስ 9፥27-30

ኢየሱስም ከዚያ ሲያልፍ ሁለት ዕውሮች። የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረን ብለው እየጮሁ ተከተሉት።…ኢየሱስም። ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን? አላቸው። አዎን፥ ጌታ ሆይ አሉት። እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ። [ያመንሁትን ነው የምሆነው!]።

---

## ዮሐንስ 17፥3

እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን [እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ጥቅም የሚመጣው ከእርሱ ጋር ባለኝ ኅብረት/የቅርብ-ግንኙነት እድገት ውጤት ነው] ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።

## ፊሊጵስዩስ 4፥8

… እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስባለሁ፤ [ከእነዚህ በተቃራኒ ላይ ሳይሆን በእነዚህ ላይ አዕምሮዬን አተኩራለሁ/አሰናዳለሁ!]።

## ማቴዎስ 6፥10

መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ [በመንግሥተ ሰማይ ምንም ሕመም የለም]።

## ዮሐንስ 14፥12

ኢየሱስ እንዳለ፡- በእርሱ ካመንሁ እርሱ የሚያደርገውን ሥራ እኔ ደግሞ አደርጋለሁ፤ ከዚህም የሚበልጥ አደርጋለሁ፥ …

## መዝሙር 27፥1

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ [ፈውሴ፣ ድኅነቴ/መዳኔ፣ ጥበቃዬ] ነው፤ ስለዚህ ለምን እፈራለሁ?

## ኦሪት ዘዳግም 28፥1-2፤ 7

… የአምላኬን የእግዚአብሔርን ቃል ብሰማ፥ ዛሬም ያዘዘኝን ትእዛዙን ሁሉ ባደርግ ብጠብቅም አምላኬ እግዚአብሔር ከምድር አሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያደርገኛል።

የአምላኬንም የእግዚአብሔርን ቃል ብሰማ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልኛል፤ ያገኙኝማል። የአምላኬንም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቻለሁና እግዚአብሔርም በላይዬ የሚቆሙትን ጠላቶቼን [ሕመሞችን] በፊትቴ የተመቱ ያደርጋቸዋል፤…

## መዝሙር 118፥17

አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ።

## 1ኛ ጴጥሮስ 2፥24-25

.. በመገረፉ ቁስል ተፈውሻለሁ።

## መዝሙር 107፥20

ቃሉን ላከ ፈወሰኝም፥ …

## መዝሙር 92፥14

በለመለመ ሽምግልና አፈራለሁ…

## ዘዳግም 3፥22

አምላኬ እግዚአብሔር እርሱ ስለ እኔ ይዋጋልና አልፈራቸውም…

## 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥4-7፣ 8

ታጋሽ ነኝ፥ ቸርነትንም አደርጋለሁ፤ አልቀናም፤ አልመካም፥ አልታበይም፤
የማይገባኝን አላደርግም፥ የራሴንም አልፈልግም፥ አልበሳጭም፥ በደልን አልቆጥርም፤

ከእውነት ጋር ደስ ይለኛል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለኝም፤

ሁሉን እታገሣለሁ፥ ሁሉን አምናለሁ/እምነቴ አይጠፋም፥ ሁሉን ተስፋ አደርጋለሁ፥ በሁሉ እጸናለሁ።

አልወድቅም፤

# ማርቆስ 9፥23

ካመንሁ ሁሉ ይቻላል።

# የበረከት ጸሎት

ማቴዎስ 18፥19 "...ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።" ይላል



ለፈውሳችሁ በኢየሱስ ስም ከአንተ/ከአንቺ ጋር እስማማለሁ (ያ ሁለት ያደርገናል)። ተፈውሳችኋል! You are healed!

ሻሎም እና ፍቅር፥

Sid Israel Roth

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መግለጫ


## በዚህ ecመጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥቅሶችና ተጓዳኝ ትርጉሞች:



New King James
ዘጸዓት 23:25-26
ዘዳግም 3:22
ዘዳግም 7:14-15
ዘዳግም 28:1-2, 7
መዝሙረ ዳዊት 1:1-3
መዝሙር 84:11
መዝሙር 86:15
መዝሙር 91:9-10, 16
መዝሙር 103:2-3
መዝሙር 103:20
መዝሙር 105:37
መዝሙር 107:20
መዝሙር 118:17
ምሳሌ 4:20-22
መዝሙር 6:2
ኢሳይያስ 26:3
ኢሳይያስ 40:31
ኢሳይያስ 53:4-5
ኢሳይያስ 54:17
ኢሳይያስ 55:10-12
ማቴዎስ 6:10
ማቴዎስ 18:19
ማቴዎስ 28:18-19
ማርቆስ 9:23
ዮሐንስ 20:29
የሐዋርያት ሥራ 10:38
ሮሜ 8:11
ሮሜ 10:17
1ኛ ቆሮንቶስ 13:8
2ኛ ቆሮንቶስ 1:20
2ኛ ቆሮንቶስ 4:13
2ኛ ቆሮንቶስ 5:21
ኤፌሶን 3:20
ፊሊጵስዩስ 2:9-10
2ኛ ጢሞቴዎስ 1:7
ዕብራውያን 6:12
1ኛ ጴጥሮስ 2:24
1ኛ ዮሐንስ 1:9
1ኛ ዮሐንስ 3:8
1ኛ ዮሐንስ 4:4
1ኛ ዮሐንስ 4:17-18
1ኛ ዮሐንስ 5:14-15
ራእይ 12:11
Amplified
ሶፎንያስ 3:17
ማቴዎስ 6:14-15
ዮሐንስ 10:10
ዮሐንስ 14:12
ዮሐንስ 16:23-24
ሮሜ 4:17-21
ፊሊጵስዩስ 4:8
ዕብራውያን 11:1
ያዕቆብ 1:2-4, 12
ያዕቆብ 4:7
2ኛ ጴጥሮስ 1:3-4
Wuest
ማቴዎስ 12:36-37
ማቴዎስ 16:19
ሉቃስ 10:19
ዮሐንስ 17:3
ሮሜ 4:17-21
ዕብራውያን 11:6
New Living Translation
ኢያሱ 1:7-8
መዝሙር 27:1
መዝሙር 92:14
ማርቆስ 9:23
1ኛ ቆሮንቶስ 13:4-7
ገላትያ 6:9
1ኛ ጴጥሮስ 3:9
መልዕክት
ማቴዎስ 9:27-30
One New Man
አንድ አዲስ ሰው
ማርቆስ 11:23-24

# እንድታነቧቸው የሚመከሩ ምንጮች

ከተፈጥሮ በላይ ለሆነ ፈውስ በተጨማሪ ለማደግ እነዚህን ምንጮች ተመልከቷቸው መርምሯቸው:





Stories of Supernatural Healing የእግዚአብሔርን ተዓምር አድራጊ ኃይል በተለማመዱ/በቀመሱ መደበኛ ሰዎች የሆነ የእውነተኛ ታሪኮች ስብስብ ነው። እግዚአብሔር አሁንም እየፈወሰ ነው፥ እርሱም ዛሬ ሊፈውሳችሁ ይፈልጋል!

ይህ መጽሐፍ ተስፋን ያነሣሣል፥ እምነትን ያጠነክራል፥ ለመፈወስ እና ለማደስ/ለመጠገን ያለውን የአባትን መሻት ያብራራል። እያንዳንዱ ታሪክ ድንቅ፣ ልዩ፣ እና አሳብ-ቀስቃሽ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ኅብረት እንዲኖራችሁ በሩን የሚከፍትላችሁ ነው።

እዘዙ Stories of Supernatural Healing ዛሬ here.

---




በ Healing Rivers, ከበስተጀርባ ካለው የተቀባ ሙዚቃ በተያያዥነት፥ ፈውስን ለመቀበል ያለውን ቁልፎች ሲድ ይገልጻል። እርሱ በተጨማሪ ፈዋሽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን ያነባል እናንተም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹን እንድትናገሯቸው በመሐል ቆም ይላል፥ ስለዚህ እናንተ መስማማትና ፈውሳችሁንና ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥርመሳን ማወጅ ትችላላችሁ።

ስታመልኩና ወደ ተካተቱት የሙዚቃ ስብስቦች ውስጥ ስትጠመቁ፥ የእግዚአብሔርን የፈውስ ኃይል ትለማመዳላችሁ እና እርሱ ለእናንተ ያለውን የተስፋ ቃል ትቀበላላችሁ።

እዘዙ Healing Rivers ዛሬ here.

በፈውስ ላይ ያለውን ጠቅላላ የሪሶርሶች መዝገባችንን ብ'ራውዝ አርጉ: sidroth.org/store/products/supernatural-healing

# ታሪካችሁን አካፍሉ

በዚህ eመጽሐፍ እንዴት እንደተባረካችሁ ወይም እንዴት ፈውሳችሁን እንደተቀበላችሁ ንገሩን:

https://www.facebook.com/its.supernatural

https://twitter.com/sidrothtv

**የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ የእግዚአብሔር አብ ቃልና ልጅ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** የባሪያውን የቶማስ ቶሙከዳህታን አካል ተጠቅሞ:ተረጎመው።

hithomasgetachew@gmail.com